

ኅዳር፩÷ ፳፻፪ዓ. ም.

**በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤ አሓዱ አምላክ።**
**በስማ ለእግዝእትነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥ እምነ ወንግሥትነ**
**ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።**
**በኃይለ መስቀሉ፡ ለእግዚእነ፥ ወአምላክነ፥ ወመድኃኒነ፥ ካህንነ፥ ወንጉሥነ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ።**

ይድረስ፡ እጅግ ለተከበርክና ለተወደድክ እንዲሁም ለምትናፈቀዉ የመንግሥተ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ አገልጋይ ኪዳናዊ ወንድሜ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ!

ከተከበረችዉና ከምትወደደዉ ባለቤትህ ከኪዳናዊት እህቴ እመቤት ራሔል ዘካሪያስና ከኪዳናዊያንና ኪዳናዊዉያት ቤተሰቦችህ ጭምር እንደምን ሰንብታችኋል? እኔ ቸሩ እግዚአብሔር መድኃኔዓለም ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ጋር የተመሰገነ ይሁን ከኪዳናዉያን ቤተሰቦቼ ጋር እጅጉን ደህና ነኝ፡፡

ጋሽዬ በጥቅምት ፲÷፳፻፪ ዓ.ም የላክልኝ አጽናኝና አበረታች እንዲሁም የአገልጋይነት ስሜት እንዲሰማኝ ሳደረከዉ ቃል እግዚአብሔር ይስጥልኝ እላለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በእኔ አንቱታ አጠራር ቅር ሳትሰኝ ከእግዚአብሔር የሆነዉን፤ የራስን ሥጋና ደም አቋምና አስተሳሰብ አስተካክሎ እንደ ቅዱስ ጴጥሮሰ መቀበልና በተግባር ማወል እንዲሁም እንደ ቅዱሱ ኪዳን ምግባርና ሥርዓት መኖርና መመሳሰስ እንዳለብን ለሰጠኸኝ ምላሽ በድጋሜ ቃለ ሕይወት ያሰማልኝ እላለሁ፡፡ ልማድ ከጨከኑበት ቀላል መሆኑን ይኸዉ ይህን ደብዳቤ ስጽፍ ተረዳዉ፡፡ ልክ ለምወደዉ ታላቅ ወንድሜ እንደምጽፍ ስሜት ነዉ የተሰማኝ፡፡ ነገር ግን ልማድ ከእእምሮ ዉስጥ ቶሎ አይጠፋምና ልክ አንድ ኪዳናዊ ወንድማችን አንተ እያለ በመሃል በአንቱታ እንደጠራ ሁሉ በጽሑፍ ሆነ በንግግር ሳናስበዉ ቢደባለቅብን ወደ ኋላ ለመመለስ አስበን ሳይሆን ባለማወቅ መሆኑን እንደምትረዱልን አምናለሁ፡፡ ሌላዉ ደግሞ "ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም" የሚለዉ መለኮታዊ ቃል ማንኛዉም እዉነተኛ የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ሁሉ ለእግዚአብሔራዊዉ ሥርዓትና አጠራር እንዲሰለፍ ያደርጋል፡፡

የልጆቻንን ስመ ክርስትና ስትዘረዝር በግንቦት፳፬÷፳፻፩ዓ.ም የተወለደችዉና በወቅቱም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክታችሁን ያደረሳችሁን የአራተኛ ልጃችን ስመ ክርስትናዋ ፍቅርተ ሚካኤል የዓለም

ስሚ <u>**ማክዳ**</u> አልተጠቀሰችምና ከልጆቻችን ስም ዝርዝር ዉስጥ እንድታስገቡልን በትህትና እየጠየኩ መስከረም ፲፯÷ ፳፻፲፯ዓ.ም የተወለደዉ  አምስተኛዉ ልጃችንና የመጀመሪያዉ ወንድ ልጃችን ስም አገባለሁ፡፡ የክርስትና ስሙ <u>**ብርሃነ መስቀል**</u> ሲሆን የዓለም ስሙ ደግሞ <u>**ሕሩይ**</u> ብዬዋለሁ፡፡

ስለቤተሰቤ ጉዳይ ይህን ካልኩ ከዚህ በታች ደግሞ ሥጋዊ ባሕርያት በሚል አርዕስት  በክፍል ሁለት ሳይ ከ፴፯ እስከ ፶፫ ደቂቃ ድረስ በአንተ በኩል የተገለጹ መሳሾች ሕሊናዬን በጥያቄ የሞገቱና ሌላ ሰዉ " ንቡረ ኤርምያስ እንዲህ አሉ" ቢለኝ " ተሳስተህ ይሆናል እንዲህ አይሉም ምናልባት በተሳሳተ መልኩ ተረድተህ ይሆናል እንጂ እሳቸዉ ከልጅነት ጀምሮ ስለ ቅዱሱ ኪዳን ተጋድሎ እያደረጉና የእግዚአብሔርን ቃል በቀጥታ የሚያስተላልፉ በጠበበዉ መንገድ የሚመላለሱና ሌሎችም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በምታስገባዉ በጠባቧ መንገድ እንዲመላለሱ የሚያደርጉና ለዚያ ብቃት ለማድረስ ማንኛዉንም አገልግሎትና ድጋፍ የሚያደርጉ ናቸዉ እንጂ አህዛብና መናፍቃን እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ሲያቅታቸዉና ሌሎችን በሰፊዉ መንገድ ለማስገባትና ቁጥራቸዉን ለመጨመር ሲሉ እንደሚያደርጉት ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ በእርሳቸዉ አገልግሎት ዉስጥ አንዳች አይቀየጥም" በማለት ነበር ምላሽ የምሰጠዉና ምን እንደተባለ በራሴ ለመስማትና ለማረጋገጥ የምሄደዉ፡፡

በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የምትሰጠዉን በጽሑፍ ሆነ በመጻሕፍት እንዲሁም በድምፅና በምስል ተደግፈዉ በተለያየ መንገድ የሚተላለፉትን መልክታትን ሆነ ምላሽ እንደ አቅሜ በንቃት የምከታተል ሲሆን፤ እስከ አሁን ያነበብኳቸዉ ሆነ ያዳመጥኳቸዉ እግዚአብሔር በአንተ ላይ አድሮ ለትዉልዱ ከእርሱ የሆነዉን እያስተላለፈ መሆኑን ነዉ፡፡

ሕሊናዬን የሞገተዉንና የፈተነዉን እንዲሁም እረፍት አልሰጥ ያለዉን ጥያቄና ሐሳብ ከማቅረቤ በፊት ቀዳሚ ስሜቴን እገልጻለሁ፡፡ ዉሃ ከታች ወደ ላይ እንደማይፈስና  እንዲሁም ልጅ እናቷን ምጥ እንደማታስተምር  ሁሉ ለአንተ ለትሁትና ቅን፥ ለእዉነተኛና ታማኝ፥  ለትጉህና ለቆራጥ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ «ተሳስተሃል፥  ትክክል አይደለህም» ለማለት የምደፍርበት አቅምና ብቃት የሌለኝ ቢሆንም፤ በእግዚአብሔር የእዉነት አገልግሎት ዉስጥ በቅንነትና በእዉነት ግልጽ ያልሆነልንን መጠየቅ ፥  ቅንና እዉነት የመሰለንን መግለጽ፥ ቅሬታችንን በግልጽ ማቅረብና መወያየት፥ መመካከርና መተራረም እንዳለብን በቃልም፥  በመጽሐፍም የምታስተምረዉና የምትለዉ ስለሆነ ማብራሪያ በመጠየቄ ቅር እንደማትሰኝበኝ በመተማመንና አስተሳሰቤም ስህተት ሆኖ ከተገኘ ማረሚያ እንደምትሰጠኝ  እንዲሁም ያልተገለጸልኝ ነገር ካለ  እንደምታብራራልኝ በማመን ነዉ ጥያቄዬንና ሐሳቤን የማቀርበዉ፡፡

ሌላዉ ወደ ጥያቄዬና ሐሳቤ ከመምጣቴ በፊት ሌላኛዉን ስሜቴን እገልጻለሁ:: ይኸዉም ከተለያየ አቅጣጫ ለሚመጣልህ የተለያየ የጽሑፍ ሆነ የስልክ ጥያቄ፥ ትችት፥ ተቃዉሞ፤ በትዕግስት፥ በትጋት፥ በብቃት ካለመሰልቸት መመለስ በመቻልህና «በምን ጊዜዉ ነዉ ከተለያየ አቅጣጫ የማጎርፍለትን ጉዳይ ምላሽ የሚሰጠዉ?» በማለት በአንክሮ እጠይቃለሁ:: ሌላዉ ደግሞ ለቃለ መጠይቅ በምትሰጠዉ ምላሽ ለአንድ ለምትጠየቀዉ ጥያቄ ለብዙ ደቂቃትና ከአንድ ሰዓት በላይ ጭምር አንዳች ድካምና የሐሳብ መፋለስ ሳይታይብህ ስትመልስና እንኳን በቃል አይደለም ከመጽሐፍ እያነበቡ በዚያ መልኩ መመለስ በማይቻልበት ሁኔታ አንተ እያነበበ ከሚመልሰዉ በላይ ምላሽ መስጠትህን ስመለከት የእግዚአብሔርን ስራ አደንቃለሁ ስለስጦታዉም አመሰግነዋለሁም:: ያንተንም ችሎታና ብቃት እንዲሁም ለዚያ ጸጋ መብቃት አደንቃለሁ::

በማስከተል ደግሞ የሥጋ ባሕርያት በሚል አርዕስት በክፍል አንድና ሁለት ከጋብቻና ከሥጋ ፍትወታት ጋር በተመለከተ በቀረበዉ ምላሽ ላይ ያገኘሁትን እዉነተኛ ምላሽና የእግዚአብሔር እዉነት በራሴ የመረዳት አገላለጽ ከብዙ በጥቂቱ አቀርባለሁ :: ኪዳነ አዳም ወሔዋን ጠብቀዉ የሚኖሩት የኢትዮጵያዉያን የጋብቻ ሥርዓት በእግዚአብሔር የተፈቀደና የታዘዘ መሆኑን:: በጋብቻ የሚፈጸም የግብረሥጋ ግንኙነት የከበረና አንዳች ርኩሰት ሆነ መጥፎነት እንደሌለዉ:: እንዲሁም የወንድ የዘር ፍሬ ሆነ የሴት ወር አበባ እግዚአብሔር በወንዱና በሴቷ ላይ እንዲከሰት ያደረገዉ የእርሱን ፍጥረትና ልጆች የሆኑትን የሰዉ ልጆች ካለመኖር ወደመኖር እንዲመጡ ለማድረግ በመሆኑ አንዳች ርኩሰትና ጸያፍነት እንደሌለባቸዉ፥ በመልካምነት ብቻ እንድንቀበለዉና የተሳሳተ አስተሳሰባችንን እንድናስተካክል:: በእስራኤላዉያንና በግብጻዉያን ተጽህኖ ዉስጥ የወደቀዉንና በትዉልዱ የሰረጸዉን የተሳሳተ አስተሳሰብ ማስተካከል እንዳለብን:: ሥልጣነ ክህነትን በራሳቸዉ ስር ለመቆጣጠር ሲሉ ግብጻዉያን በምንክስና ስም በኢትዮጵያዉያን የክህነት አገልግሎትና ሥልጣን ላይ እንዲሁም በትዉልዱ አስተሳሰብ ላይ ምን ያህል አሉታዊ ተጽህኖ እንደፈጠሩ ወዘተ ነዉ ::

ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት በተለያየ ምክንያት የተረገዙ ህፃናት እንዲወለዱና በወላጅነት የሚያሳድጓቸዉ ከሌለ ተቀብላ አስፈላጊዉን እንደምትፈጽምላቸዉ የሚገልጸዉን የምስራች መልእክት በደስታ እቀበላለሁ:: ምክንያቱም ሰዉ በሥጋ ድካም ሆነ በፈተና በመዉደቅ እንዲሁም በመገደድ ግብረ ሥጋ ግንኙነት ፈጽሞ ጽንስ ቢይዝና ፅንሱን ቢያስወርድ እንደነፍሰ ገዳይ ተቆጥሮ ይፈረድበታል፤ ስለ ዘማዊነቱና አመንዝራነቱም በተጨማሪ ይፈረድበታልና ከባሰ ፍርድ

እንዲድንና ያ በዚያ መልክ እንዲወለድ የተፈረደበት ሕጻን ደግሞ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጅ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ዉጭ ማንም በሕይወቱ ሊፈርድበት አይገባምና ነዉ፡፡ ነገር ግን ከጋብቻ በፊት ሆነ ከጋብቻ በኂላ የሚፈጸመዉን የዝሙትና የአመንዝራነት ተግባር አወግዘዋለሁ፡፡ በዚያ የሞተ ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሰዉንና የተመላለሰዉንም ንስሐ እንዲገባ ወንድማዊ ምክሬንና ትምህርት እሰጠዋለሁ እንጂ እንደ ስህተት እንዳይመለከተዉና ኃጢአት እንዳልሆነ አድርጎ እንዳይቆጥረዉ አልመክረዉም፤ አላስተምረዉም፡፡

ሌላዉ በሕጋዊ ጋብቻ የተወሰኑ ካህናት ከማንም በላይ እንደ ችሎታቸዉና እዉቀታቸዉ በኃላፊነት ቦታ መቀመጥና ማገልገል ሲገባቸዉ ለሥልጣን ሲሉ ሕይወቱ ሳይኖራቸዉ ቆብ ብቻ በመድፋት በከፍተኛዉ የክህነት ወንበር ላይ የጠቀመጡ ነገር ግን የዓመፃ፥ የክህደት፥ የአምልኮ ምንዝርና የሚፈጽሙ እንዲሁም በዝሙት ሕይወት ዉስጥ የሚልከሰከሱ አስመሳይ አገልጋዮችን ባልተገባቸዉ ወንበር ላይ ስመለከት ምናለ እግዚአብሔር ለትዉልዱ በፈቀደዉና ባዘዘዉ ጋብቻ ተወስነዉ ከግብጽ ኦርቶዶክስ ተጽህኖ ነጻ ሆነዉ በእግዚአብሔራዊዉ ሥርዓት ቢመላለሱና ቢያገለግሉ ኖሮ ሌላዉንም ሳያሰናክሉ መልካም ፍሬ ማፍራት ይችሉ ነበር እላለሁ፡፡ እንዲሁም ምንኩስናቸዉንና ክህነታቸዉን አክብረዉ የሚኖሩና የሚያገለግሉ መነኮሳት ፥ ቀሳዉስት ፥ መሪጌቶች፥ መምህራን፥ ዲያቆናት፥ ሰባክያን ፥ ዘማሪያን እንዳሉ ሁሉ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ ከጳጳሳት፥ ከቀሳዉስት(ከቄስሶች) ፥ ከዲያቆናት፥ ከመምህራን፥ ከመሪጌቶች፥ ከዘማሪያን ፥ ከሰባክያን ሳይቀር እግዚአብሔር ብቻ አይደለም ብዙ ምእመናንና እዉነተኛ አገልጋዮች የሚያዉቋቸዉ በዝሙትና በአመንዝራነት የሞት ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱ አሰናካዮችና የእዉነት እንቅፋቶች የሆኑ አስመሳይ አገልጋዮች አሉ፡፡

ከዚህ በማስከተል ወደ ፍሬ ሐሳቤ እገባለሁ፡፡ ሕሊናዬን የፈተነዉና የሞገተዉ ምላሽህን ያዳመጥኩት ሥጋዊ ባሕርይ በሚል በክፍል ሁለት ከ፴፯ተኛዉ እስከ ፶፭ተኛዉ ደቂቃ የተሰጠዉ ምላሽ ነዉ፡፡ እንዴት እንዲህ ሊሆን ይችላል? በእዉነተኛዉና በጠባቡ መንገድ ተመላልሰንና ኖረንበት ለማያልፈዉ ሰማያዊ መንግሥት እንድንበቃ ታላቅ ተጋድሎ እያደረገ፤ ያ ብቻ አይደለም በምድራዊ ሕይወታችንም በሰላም፥ በፍቅር፥ በጤና እንድንኖር የሚያስችለዉን እግዚአብሔራዊ ትምህርት እየሰጠን እንዲሁም ሰይጣናዊ ትምህርትና የሞተ ሕይወት እያወገዘ እንዴት ዝሙትና አመንዝራነት የሚስፋፋበትን ምላሽ ሊሰጥ ቻለ? ወይስ በተሳሳተ መንገድ ተረድቼዉ ይሆን? ወይስ ያልገባኝ ነገር ይኖር?» በማለት ሕሊናዬ ያወጣል፤ ያወርዳል፡፡

«እኔ ሕግና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር  አልመጣሁም፡፡ እዉነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የዉጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ፡፡ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰዉም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰዉ በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፡፡ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል፡፡» ማቴ ፭÷ ከ፲፯ እስከ ፳የሚለዉን የጌታ ትምህርት የሚያስተምረዉ ጋሽዬ እንዴት ያንን ምላሽ ሊሰጥ ቻለ ብዬ ሕሊናዬ እስከአሁን ይጠይቃል፡፡

«<u>አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል</u>፡፡ ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አዉጥተህ ከአንተ ጣላት ሙሉ ሰዉነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት ሙሉ ሰዉነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃል፡፡

ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፡፡ የተፈታችዉንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፡፡» ማቴ ፭÷ ከ፳፯ እስከ ፴፪ የሚለዉን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት የሚያስተምረዉ እንኳን ዝሙትና አመንዝራነት በተግባር ሊፈጸም ቀርቶ በሐሳብ እንኳ መታሰብ እንደሌለበት የሚገልጸዉን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ እያወቀ እንዴት ትዉልዱ ዝሙትን ሆነ አመንዝራነትን እንደ ኃጢአትና እንደ ስህተት እንዳይቆጥር የሚያደርግ ምላሽ ሊሰጥ ቻለ በማለት ሕሊናዬ  ግራ ተጋባ፡፡ ምክንያቱም ከጋብቻ በፊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደ ኃጢአትና እንደስህተት የማያስቆጥር ከሆነ ማነዉ ራሱን ከዝሙት ጠበቀ ከነክብረንጽህናዉ ለጋብቻ የሚበቃዉ? እንኳን እንዲህ ተብሎ አይደለም ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ነዉ እየተባለ፤ በጋብቻ ላይ የሚፈጸም ግብረ ሥጋ ግንኙነት አመንዝረኛነት ኃጢአት ነዉ ያስኮንናል እየተባለ እንኳ ፤ ትዉልዱ ራሱን ሊገዛና ከዝሙትና ከአመንዝረኛነት ሊለይ አልቻለም፡፡ ታዲያ ይህ ነጻነት ከተሰጠዉ ትዉልዱ በዝሙትና በአመንዝረኛነት ተግባር አይመላለስምን? ገና ከሕፃንነታችን ጀምሮ በሐሳብ፥ በንግግር፥  በተግባር የሚፈትነን ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጭምር በሕሊናችንና በአካላችን ላይ በመንገሥ የፍትወት ስሜታችንን እየቀሰቀሱ ካገኘናት ወይንም ካገኘነዉ  ሰዉ ጋር ግብረሥጋ ግንኙነት

እንድናደርግ በማድረግ ለበሽታና ለሲኦል አይዳርጉንም ወይ? ምክንያቱም የዉስጣችን ስሜት አስገድዶን የምንፈጽመዉ ተግባር እንደ ስህተትና እንደ ኃጢአት የማይቆጠር ከሆነ የሥጋና የደም ስሜታችን ሲያይልብን እንደ እንደ እንስሳ እንደምንሆን እንዲሁም የሰይጣናት ፈቃድ ሲያይልብን እንደአዉሬና እንደ ራሳቸዉ ሰይጣናት እንደምንሆን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በተጻፉት መጻሕፍቶችህ አልገለጽክልንም ወይ?

ታዲያ የትኛዉ ትዉልድ ነዉ የራሱን ሥጋና ደም ስሜት እንዲሁም የሰይጣናትን ፈቃድና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ ይህ እግዚአብሔር የፈቀደዉ ስሜት ነዉና እንዲህ ልፈጽም፤ ይህ የሥጋና ደም ስሜቴ ነዉ ፥ ይህ የሰይጣናት ፈተና ነዉ አልፈጽምም በማለት ራሱን የሚገዛዉ? እንደምታዉቀዉ ትዉልዱ የተፈቀደለትን የወንድና የሴት ግንኙነት ትቶ ወንድ ከወንድ ሴት ከሴት ግንኙነት በማድረግ ላይ አይደለም ወይ? ለምን እግዚአብሔር ያልፈቀደዉን ትፈጽማለህ፥ ትፈጽሚያለሽ ተብሎ ሲጠየቅ « ዲሞክራሲ መብቴ ነዉ፤ ነጻነቴን ማንም ሊከለክለኝ አይችልም የሚል ጠማማ ትዉልድ ነዉ እኮ ይለዉ:: ያ ብቻ አይደለም ትዉልዱ ሕሊናዉን ለዲያብሎስ መንፈስ አሳልፎ በመስጠቱ አባት ልጁን የሚደፍረበት ዘመን ደርሰናል፤ ዘመድ ከዘመዱ የሚገናኝበት ዘመን ደርሰናል:: የዝሙት አዳሪነት ተግባር እንደ መደበኛ ስራ ተቆጥሮ ከገጠር እስከ ከተማ ድረስ በየቦታዉ የዝሙት ተግባር ተስፋፍቷል::

ራሱን የሚገዛና ሕሊናዉ መንፈስ ቅዱስ ብቻ የሚመራ አንድ ፐርሰንት የሚሞላ ትዉልድ አለ ወይ? «ይህ ከእግዚአብሔር ነዉ፥ ይህ ከዲያብሎስ ነዉ፥ ይህ ከሥጋና ደም ስሜት ነዉ» ብሎ በሕሊናዉና በሰዉነቱ የሚከሰተዉን ስሜት በመለየት በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ የሚጸነ ሰዉ አለ ወይ? በጣት የሚቆጠሩ ቢኖሩ እንኳ ለእነሱ የሚሰጠዉ ትምህርት ሌላዉ ዓመፀኛ፥ ከሃዲና አመንዛሪ ትዉልድ ለራሱ ፍላጎት ማርኪያ በማድረግ ሊጠቀምበትና ሊሰናከልበት አይችልም ወይ? ስለምን በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እግዚአብሔር ቃልና እንደ ጠባብ መንገድነቷና « ከቃልህ የተነሳ ትጸድቃለህ ከቃልህ የተነሳ ትኮነናለህ» ያለዉን አምላካዊ ቃል በመከተል እንኳን በተግባር ኃጢአት መፈጸም ይቅርና ከንግግርና ከሐሳብ ኃጢአት መከልከል እንዳለብን በአጽንኦት ሊገለጽልን አይገባም ወይ?

ከላይ ሕሊናዬ የታወከበትና እንዴት ሊሆን ቻለ የሚለዉ ጥያቄ የተነሳዉ በክፍል ሁለት የቃለ መጠይቅ መላሽህ ላይ «ምናልባት ከቻልን ሌላዉን ስሜታችንን እንደምንቆጣጠር እስከ ጋብቻ ድረስ

ከግብረ ሥጋ ግንኙነት መታቀብ፤ ካልቻልን ግን ከጋብቻ በፊት ግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢደረግ እንደተሳሳትን መቁጠር የለብንም» የሚለዉ ምላሽ ነዉ። እኔ እስከዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ ቅድስት ቤተክርስቲያን አስተምሮ የማዉቀዉና አምኜዉም የተቀበልኩትና ለሌላዉም እያስተላለፍኩ ያለዉት ከጋብቻ በፊት እንኳን ከማይመለከታቸዉ ከተለያዩ ሴቶች ጋር ይቅርና ከእጮኛችን ጋር እንኳ እስከ ጋብቻችን ድረስ  ግብረሥጋ ግንኙነት መፍጠር እንደሌለብን ነዉ። ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ግብረሥጋ ግንኙነት ንስሐ የሚያስፈልገዉና እንደ ዝሙት የሚቆጠር መሆኑን ነዉ። እኔም ከጋብቻዬ በፊት ከተለያዩ ሴቶች ጋር ግብረሥጋ ግንኙነት በመፈጸሜ ስለ ዝሙት ተግባሬ ንስሐ የገባሁ ቢሆንም ድንግልናቸዉን በማክበራቸዉና እስከ ጋብቻ ቀን ድረስ ስሜታቸዉን በመቆጣጠር የድልና የክብር አክሊል የሆነዉን ተክሊል የሚያደርጉትን ሳለደርግ ነዉ ለመንግሥተሰማያት የሚያበቃኝንና ኃጢአቴን የሚደመስስልኝን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን ብቻ በመቀበል ጋብቻዬን የፈጸምኩት።

ታዲያ ከጋብቻ በፊት የሚደረግ ግብረ ሥጋ ግንኙት እንድስህተትና ኃጢአት የማይቆጠር ከሆነ ስለፈጸምኩት ግብረሥጋ ግንኙነት መጸጸት ሆነ ንስሐ መግባት አይገባኝም ነበር ማለት ነዉን? እንዲሁም ክብረድንግልናቸዉን ጠብቀዉ ተክሊል እንደሚያደርጉት እኔም የድል አክሊል ይገባኛል በማለት ተክሊል ባደርግ የተገባሁ ነበር ማለት ነዉን? በእርግጥ ሕይወትን ከማግኘት አንጻር ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙ የሚበልጥ ቢሆንም ሰማዕታት፥ ነቢያት፥ ሐዋርያት ታላቅ ተጋድሎ በማድረጋቸዉ ምክንያት ከሌሎች የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሚወርሱ ጻድቃን በተለየ ሁኔታ የድል አክሊል ሲደረግላቸዉ ሌሎቹ ጻድቃን ለእኛም ይገባናል እንደ እደማይሉ ሁሉ እኔም ድግልናዬን ጠብቄ አልተገኘሁምና የድልና የክብር አክሊል የሆነዉን ተክሊል ላድርግ አላልኩም። ዋጋ ላልከፈልኩበት ዋጋ ይገባኛል አላልኩም።

ትዉልዱ እንኳን ከጋብቻ በፊት ግብረሥጋ ግንኙነት ብትፈጽሙ ኃጢአት አይደለም እንደስህተት አይቆጠርም ተብሎ አይደለም ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ነዉ ያስኮንናል፥ በምድርም ለተለያየ በሽታ ያጋልጣል እየተበለ እንኳን ትዉልዱ ከዝሙት ሊጠበቅ አልቻለም። ይልቁኑ ዝሙቱም አልበቃ ብሎት መብቴና ነጻነቴ መጠበቅ አለበት እያለ በግብረሰዶም ርኩሰት በሞት ሕይወት ዉስጥ ይመላለሳል። መንግሥታትም ለእግዚአብሔር ቃል አንዳች ቦታ ሳይሰጡ ትዉልዱ በዝሙት ሕይወት ዉስጥ እንዲጸና በማድረግ ነገር ግን ለሥጋዊ በሽታ እንዳይዳረጉ ብቻ ኮንደምንና ሌሎች መጠቀሚያዎችን እንዲጠቀሙ በተለያየ ሚዲያ ቅስቀሳ ያደረጋሉ። ታዲያ ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ግብረሥጋ ግንኙነት የእግዚአብሔርን ቃል ማለትም« አትዘሙት፥ አታመንዝር» የሚለዉን እንደ

መተላለፍ የማይቆጠር ከሆነ ማነዉ ታዲያ ድንግልናዉን ጠብቆ ለጋብቻ የሚበቃዉ ? ያ ብቻ አይደለም ማንም ሰዉ የፍትወት ስሜቱን ከሚፈልገዉ ሰዉ ጋር ማርካት ከተፈቀደለት ማነዉ ጋብቻን ናፍቆ በትዳር መወሰንን የሚፈልግ? ያ ብቻ አይደለም ማነዉ የመጀመሪያዉን ቅዱሱን ኪዳን ጠብቆ የሚገኝ?

በታላቁ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት እንኳን በተግባርና በንግግር ዝሙት መፈጸም ቀርቶ በሐሳብ እንኳ ሰዉ ዝሙትን እንዳያስብ«አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፡፡» የሚለዉን ማጽናት ሲገባን ከሕጋዊ ጋብቻ ቢፊት ሆነ ከጋብቻ በኋላ የሚፈጸም ዝሙትንና አመንዝራነትን ዉስጣችን ተገደን የምንፈጽመዉ ከሆነ እንደ ስህተት መቆጠር የለበትም ካልን «እንኳን ዘንቦብሽ ድሮም ጤዛነሽ» እንደሚባለዉ ትዉልዱ ይህን ነጻነትና ሰፊ መንገድ ካገኘ በሁለት ልብ ያለዉ ብቻ አይደለም ራሱን በጸሎት፥ በጾም፥ በስግደትና በእግዚአብሔር ቃል በመግዛት ከዝሙትና ከአመንዝራነት እየጠበቀ ያለዉ ሰዉ ጭምር «ለምን ስሜቴን በመቆጣጠር እፈተናለሁ፥ ራሴን አስጨንቃለሁ ከጋብቻ በፊት ግብረሥጋ ግንኙነት ማድረግ እንደስህተትና ኃጢአት ካልተቆጠረ የፍትወት ስሜቴን እንደምፈልገዉ አረካለሁ» ማለቱ አይቀርም፡፡

እንኳን ትዳር የሌላቸዉ ይቅርና ትዳር ያላቸዉ ጭምር አይናቸዉ ይቀላዉጣል፤ ያንቺንም ያንንም ይመኛል፡፡ ከተመቻቸላቸዉም አጋጣሚዉን በመጠቀም ግብረ ሥጋ ግንኙነት ይፈጽማሉ፡፡ በዚህም ያልተፈለገ እርግዝና ይመጣል፡፡ ያኔ «ከምዋረድ ጽንሱን ላስወርድ» ወደሚለዉ ዉሳኔ ይደረሳል፡፡ ወይንም ጽንሱ ከገፋ ይወለድና የትም ይጣላል፡፡ ታዲያ ይህ ክስተት እንዳይፈጠር የአምላካችንን ቃል በማጽናት «ማንም ይሁን ማን ከጋብቻ በፊት ሆነ ከጋብቻ በኋላ ዝሙትንና ማመንዘርን መፈጸም ቀርቶ ማሰብ እንደሌለበት ልናስተምረዉ አይገባም ወይ? ስሜቱ ገፋፍቶትና አስገድዶት የሚፈጽመዉ ግብረሥጋ ግንኙነት እንደ ስህተትና ኃጢአት እንዳይቆጠር ሊመከርና ሊበረታታ ይገባል ወይ? በርግጥ በዝሙትና በአመንዝራነት የወደቀ ወንድ ሆነ ሴት ድርጊቱ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንደመተላለፍ ቆጥሮ ይኸዉም «አታመንዝር፥ አትዘሙት» የሚለዉን ዘላለማዊዉን ቃል መተላለፉን አምኖና በዓመፃ ሕይወት መመላለሱን ተገንዝቦ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለስና ራሱን ለቅዱስ ሥጋዉና ደሙ እንዲያበቃ ሊመከር፥ ሊበረታታ፥ ትምህርት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ያ ብቻ አይደለም ጽንስ ያስወረዱትም ቢሆን ራሳቸዉን እንደነፍሰ ገዳይ ቆጥረዉ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ ጥሪ ሊቀርብላቸዉ፥ ሊመከሩ፥ ትምህርት ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በሥጋ

ድካም በፈተና በመዉደቅ፥ ባለማወቅ እና  በመገደት ፈጽሞዉት ይሆናልና። ጌታም በወንጌሉ ያንቺ ዘማዊ ሴት «ዳግም እንዳትበድይ» በማለት ነዉ ያሳለፈችዉን የዘማዊነት የዓመፃ ተግባሯን ይቅር ያላት። ነገር  ግን ተግባሯ ትክክል ባለመሆኑ ዳግም በዚያ ተግባራ እንዳትመላለስ አስጠንቅቋታል እንጂ እንደ ስህተትና እንደ ኃጢአት እንዳትቆጥረዉ አላደረገም።

ሌላዉ ምንም እንኳን ከጋብቻ በፊትና ከጋብቻ በኋላ በዝሙትና በአመንዝራነት የሚረገዙ ልጆች ምንም ይሁን ምን ማዉጣትና መገደል እንደሌለባቸዉ ያሳሰብከዉና ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ተቀብላ እንደምታሳድጋቸዉ የገለጽከዉ የምስራች፤ ንስሐን የሚቀበለዉን የእግዚአብሔር ባሕርይ መላበስህንና የእርሱን መንገድ መከተልን የሚያመላክት ሲሆን፤ ነገር ግን እነዚያ ከጋብቻ በፊት በዝሙት የወደቁትና እንዲሁም በጋብቻ ላይ እያሉ አመንዝራነትን የፈጸሙ ሊገሰጹ የሚገባና ወደንስሐ እንዲመለሱ፥ ዳግም በዝሙትና በአመንዝራነት ሕይወት እንዳይመላለሱ ሊመከሩ አይገባም ወይ? ድርጊታቸዉን እንደትክክለኛ ተግባር ልንቀበለዉ ይገባል ወይ? በዝሙትና በአመንዝራነት የሚመጣ ትዉልድ መልካም ፍሬ ሊያፈራ ይችላል ወይ? ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች አይሆኑም ወይ? ለምድራዊ ሕይወት ሆነ ለሰማያዊዉ ሕይወት ማንኛዉም ቢሆን ከሕጋዊ ሚስቱ ብቻ መዉለድ እንዳለበት በአጽንኦት ማስተማር የለብንም ወይ? ለዓመፀኛ፥ለከሃዲ፥ ለአመንዛሪ ትዉልድ በኃጢአት ሊወድቅበት የሚችለዉን መንገድ ልንከፍትለት ይገባል ወይ? በጠባቧ  በር ብቻ እንዲመላለስና ተጋድሎ እንዲፈጽም ማድረግ የለብንም ወይ? እስከዛሬ የአነተን አገልግሎት ሳዉቅ እንኳን የእግዚአብሔር ትእዛዝና ሕግ ይቅርና ትክክለኛዉ ትዉፊት እና ቅርስ እንኳ ካለመቀናነስና ካለመለወጥ እንዲጠበቅ ታላቅ ተጋድሎ ማድረግህን ነዉ። በእርግጥ ከራሴ ተሞክሮ በጽሑፍና በቃል የሚገለጽ እኩል አለመሆኑን ነዉ። ምክንያቱም በጽሑፍ ነገሮችን ግልጥልጥ አድርጎ ማቅረብ ሲቻል በቃል ግን በሕሊናችን ወዲያዉ የሚመጣዉን አጭር ምላሽ ነዉ መስጠት የሚቻለዉ። በዚህ ምክንያት  ይመስለኛል ለእኔም አጭሯ ምላሽህ ሕሊናዬን የሞገተዉና እንዴት ሊሆን ይችላል በማለት ጥያቄ ዉስጥ የገባሁ።

ነፍሱን፥ ሥጋዉን፥ መንፈሱን ፍጹም ለእግዚአብሔር በማስገዛት የሚኖር ትዉልድ አንድ ፐርሰንት እንደማይሞላ ከእኔ በላይ አንተ ትዉልዱን በደንብ ታዉቀዋለህ። በዚህም ምክንያት ሌላዉ ፺፱ ፐርሰንቱ እንደ ሥጋና ደም ስሜቱ የሚመላለስና ሕሊናዉ በዲያብሎስ መንፈስ እየተመራ የሚሰራ፥ የሚናገር፥  የሚያስብ ነዉ። ይህ ትዉልድ «የዉስጥ ስሜትህ አድርግ አታድር እንደሚልህ ተመራ»

ከተባለ ራሱን በዉሸት እዉነት እያሳመነ ዓመፃ፥ ክህደት፥ ርኩሰት የሚፈጽም ትዉልድ ነዉ። ያ ብቻ አይደለም ወገኑንም ጭምር ኃጢአቱን እንደትክክለኛ ተግባር እንዲቆጥር እያስደረገ በዓመፃና በኃጢአት ሕይወት እንዲመላለስ የሚያደርግ ነዉ። ነፍሳቸዉን፥ ሥጋቸዉን፥ መንፈሳቻዉን ለእግዚአብሔር ያስገዙትን ደግሞ እንደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት፤ ከሥጋና ደም ስሜት ሙሉ በሙሉ እንዲለዩና ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸዉን እንዲክዱ፥ ስለ እዉነት እንዲመሰክሩ፥ እንዲሁም የሥጋ ፍትወታትን በተመለከተ ከጋብቻ በፊት ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ለማንም ሰዉ ግብረሥጋ ግንኙነትን እንደማትፈቅና ምናልባት በፈተናና በሥጋ ድካም ግብረሥጋ የፈጸመ ሰዉ ቢገኝ ዝሙት እንደፈጸመ ቆጥሮ በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለስና ራሱን ለጋብቻ እንዲያበቃ መምክርና መደገፍ አይገባም ወይ?

በጋብቻ ላይ ያሉ ደግሞ ከሚስታቸዉ ወይንም ከባላቸዉ ዉጭ ከማንም ሰዉ ጋር እንኳን በተግባርና በንግግር ዝሙት ሊፈጽሙ ይቅርና በሐሳብ እንኳ ቢመጣባቸዉ ሊቃወሙትና ሊጸጸቱበት እንደሚገባ በአጽንኦት ልንነግራቸዉና ልናስተምራቸዉ አይገባም ወይ? ባጠቃላይ ቅዱሱን ኪዳን ጠብቀዉ ያሉት ሁሉ ባጠቃላይ ሕይወታቸዉ ለሌላዉ ትዉልድ አርአያና ብርሃን ሆነዉ እንዲኖሩ፥ ማንንም ሰዉ እንኳን በተግባር አይደለም በንግግር እንዳያሰናክሉ በጥብቅ ሊመከሩና ሊማሩ አይገባም ወይ? ለምን የዉስጥ ፍላጎታችን አስገድዶን የምንፈጽመዉ ተግባር እንደ ኃጢአት መቁጠር እንደሌለብን ይገለጻል? ምክንያቱም ሥጋ ለባሾች ነንና ያ ብቻ አይደለም ሌት ተቀን በተግባር፥ በንግግር፥ በሐሳብ ጭምር የሚፈታተኑን እልፍ አእላፋት ሰይጣናት በሕይወታችን ዙሪያ አሉና። ሰይጣናት በተግባርና በንግግር የፈጸምነዉን አይደለም እያሰብን ያለዉን እዛዉ ሕሊናችን ጋር ሆነዉ የሚያዳምጡ ከሳሾቻችን ናቸዉና እኛ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት የምናምንና ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች የሆን ከኃጢአት መጠበቅ ያለብን ከተግባርና ከንግግር ብቻ ሳይሆን ከሐሳብ ጭምር መሆኑን ሁል ጊዜ ልንማር አይገባም ወይ? በሥጋ ድካም በኃጢአት ብንወድቅ እንኳ ኢትዮጵያ የእግዚብሔር መንግሥት በእዉነተኛ ንስሐ ከሆን የምትቀበለን መሆኑን ቢገለጽልን ይሻላል እንጂ ለፍትወት ስሜታችን መሸነፍና ያንን መሸነፍ ደግሞ እንደ ስህተት እንዳንቆጥረዉ መደረግ አለበት ወይ?

ጋሽዬ ከላይ ሐሳቤን ያቀረብኩት ጥብቅ የሆነዉ የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ላላ ተደርጎ የቀረበ ስለመሰለኝና እንደ እኔ ያሉ ደካማ ወንድሞችና እህቶች ካሉ እንዳይሰናከሉበት በማሰብ ነዉ። እንግዲህ እግዚአብሔር እና እመ አምላክ እመቤታችን ድንግል ማርያም እስከዛሬ ለጥያቄዎቼ ሆነ ለስሜቶቼ

በአንተላይ አድረዉ ምላሽ ሲሰጡኝ እንደነበረ አሁንም ሕሊናዬ ስለሞገተዉና ስለፈተነዉ ጥያቄና ቅሬታ በአንተላይ አድረዉ እንደሚሰጡኝ አምናለሁና ምላሽህን በልጅነትና በወንድምነት እንዲሁም በአገልግሎት ባልደረባነት ፍቅር እጠብቃለሁ ፡፡

በተረፈ እንደተለመደዉ  እኔንና ቤተሰቤን በጸሎታችሁ አስቡን ይላል በቅዱሱ ኪዳን አፍቃሪህና አክባሪህ፥ ልጅህና ታናሽ ወንድምህ እንዲሁም በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ባልደረባህ ፈቃደ ሥላሴ ከኪዳናዉያን ቤተሰቡ ጭምር፡፡

ወስብሓት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም

ኅዳር፲፫÷ ፳፻፲፯ዓ. ም.